በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ....................................................................................................................i

ክፍል አንድ ..................................................................................................................1

መግቢያ ..............................................................................................................1

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ ...........................................................................................1

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ...................................................................................2

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች .......................................................................2

ክፍል ሁለት ...................................................................................................................3

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣ .........................................................3

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የህሙማን አላላክና አቀባበል (ሪፈራል) ስርዓትን በተመለከተ፡- ........................................................................................................3

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ ታካሚዎችን አቀባበልና የሐኪሞች የጠዋት ስብሰባን በተመለከተ:- ..........................................................................................5

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በምልክቶችና በቀለም መለየታቸውን በተመለከተ .......................................................................................6

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚመራና የሚከታተል የሆስፒታል ቦርድ በሁሉም ሆስፒታሎች መቋቋሙን በተመለከተ ...............................................................................7

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ....8

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የላቦራቶሪ ግብዓቶችን እና መመሪያዎችን በተመለከተ፤ ........................................................................................................................10

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡ ትምህርት እና ስልጠናዎች የሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዱ መሆናቸውን በተመለከተ፡- ..................................12

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዘመናዊና በቂ የሆነ የህክምና እና የምርመራ መሳሪያዎች መኖራቸውን በተመለከተ ...............................................................13

በቂ የሆነ የመፀዳጃ ቤት፣ 24 ሰዓት የውሃና የመብራት አገልግሎት እና የኢንፌክሽን መከላከል ክፍል መኖሩን በተመለከተ ..................................................................16

ክፍል ሦስት ..................................................................................................... 20
የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)................................................................................. 20
3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው ............................................. 20
3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው.................................. 22
ክፍል አራት..................................................................................................... 24
የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)....................................................................... 24

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በኢትዮጵያ የጤናው ዘርፍ በሦስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ የአደረጃጀት እርከኖች ተደራጅቷል፡፡ የመጀመሪያው እርከን መሰረታዊ ሆስፒታሎችን የሚያጠቃልል ሲሆን እነሱም ወረዳ አቀፍ መሰረታዊ ሆስፒታል (ከ60,000- 100,000 ህዝብ የሚሸፍን)፣ ጤና ጣቢያ (ከ15,000- 25,000 ህዝብ የሚሸፍን) እና ጤና ኬላ (ከ3,000- 5,000 ህዝብ የሚሸፍን) ናቸው፡፡ ሁለተኛው የእርከን ደረጃ አጠቃላይ ሆስፒታልን የሚይዝ ሲሆን ከ1 ሚሊዮን እስከ 1.5 ሚሊዮን ለሚሆን ህዝብ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ሦስተኛው የአደረጃጀት እርከን የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚይዝ ሲሆን ከ3.5 ሚሊዮን እስከ 5 ሚሊዮን የሚደርስ ህዝብ ይሸፍናል፡፡

2. የፌደራል ሆስፒታሎች ለኢትዮጵያ የጤና አጠባበቅ ስርዓት ከሚያበረክቱት ውስጥ ለህሙማን ከፍተኛ የህክምና አገልግሎት መስጠት፣ የኢትዮጵያ ሃኪሞች የሚማሩበት፣ ልዩ ልዩ ጤና እና ጤና ነክ የሆኑ ምርምርና ጥናት የሚደረግበት፣ ለጤና ባለሙያዎች የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን የሚሰጡበት ተቋማት ናቸው፡፡

3. በኢትዮጵያ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ከ200 በላይ ሆስፒታሎች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም መካከል አስራ አንዱ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ናቸው፡፡ ከአስራ አንዱ አራቱ ማለትም ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ፣ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና አለርት ማዕከል ተጠሪነታቸው ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሲሆን የተቀሩት ሰባቱ ማለትም ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ሃረማያ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እና አዳማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል (አሰላ) ደግሞ የዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ሆነው በትምህርት ሚኒስቴር ስር ይገኛሉ፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

4. ለክትትል ኦዲቱ የተመረጡት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና ጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሲሆኑ ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጡት የህክምና አገልግሎት በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጹ ግኝቶች እና በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች (ጤና

ጥበቃ ሚኒስቴር እና ትምህርት ሚኒስቴር) ተገቢውን የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋታቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

5. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት አራት የሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ በሦስት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች (ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮለጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና ጅማ ዩኒቬርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል) ሲሆን በክዋኔ ኦዲት ግኝቶችና በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት በኦዲቱ ወቅት ከነበረው የአሰራር ክፍተት የፀዳ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለያዩ የአፈፃፀም መረጃዎችን በመከለስ፣ ለየሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቃለ መጠይቆችን በማቅረብና የህክምና ክፍሎችን፣ የላብራቶሪ፣ የፋርማሲ እና የራዲዮሎጂ ክፍሎችን በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡

6. በዚህም መሰረት በሦስቱም ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች የአገልግሎት መስጫ የህክምና መሳሪያዎች በቂ፣ ዘመናዊ እና የታካሚዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ (ታካሚዎች በሀኪሞች የሚታዘዙ ምርመራዎችን ከሆስፒታሉ እንዲያገኙ የሚያስችሉ) መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

## የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

7. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

**የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የህሙማን አላላክና አቀባበል (ሪፈራል) ስርዓትን በተመለከተ፡-**

8. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 475/1994 ንዑስ ክፍል 3(10) የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የማቋቋምና የማስተዳደር ስልጣን እንዲሁም መመሪያዎችን ማውጣት ይጠበቅበታል፡፡ይሁን እንጅ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘረጋ አገር አቀፍ የሪፈራል ስርዓት አለመኖር፣ የሪፈራል ሆስፒታሎች የእርስ በርስ ትስስር አለመኖር፣ በሆስፒታሎች ውስጥ እና በሆስፒታሎች መካከል ተናቦ መስራት (inter and intra hospital communication) አለመቻሉ፣ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ፣ አገር አቀፍ የሪፈራል መመሪያ እንዲሁም ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

9. በዚህም መሰረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንደ የሆስፒታሎቹ ስፔሻላይዜሽን ሁሉንም ሆስፒታሎች ማለትም ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ (ሶስተኛ) ደረጃ ያሉትን ሆስፒታሎች በመረጃ መረብ በማገናኘት አገር አቀፍ የህሙማን አላላክና አቀባበል/ሪፈራል ስርዓት ሊዘረጋ እንዲሁም በሆስፒታሎች መካከል የእርስ በርስ የስራ ግንኙነት እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚገባ፣የህክምና ባለሙያዎች ለታካሚዎች/ለተገልጋዩ የሚሰጡት አገልግሎት እንዲጨምር እና በስራቸው ዙሪያ የህግ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል በአገር አቀፍ ደረጃ ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ (ethical and medico-legal regulation) ሊያወጣ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

10. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ በናሙና ተመርጠው ኦዲት የተደረጉት ሦስቱም የፌዴራል ሪፌራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም፡፡

11. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል ሪፈራል ሆሰፒታሎችና የክልል ሆስፒታሎች የህሙማን አላላክና አቀባበል ሪፈራል ስረዓት ወይንም የህሙማን ቅብብሎሽ ዳይሬክትሪ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያደረጉ መሆኑን እና የታካሚዎችን መብትና ግዴታን የሚያካትትና አገልግሎቶ የት፤ እንዴት፤ በማንና

በምን ያህል ጊዜ እንደሚሰጥ የሚገልፅ የዜጎች ቻርተር በየሆስፒታሎች ተዘጋጅተውና ከህብረተሰቡ ጋር ወይይት ተደርጎባቸው ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መ/ቤታችን ከ2003- እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

12. በክትትል ኦዲቱ ወቅት የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ አገሪቱ ያወጣችውን አገር አቀፍ የሪፈራል ስርአት ደንብ እና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያዘጋጀውን የሪፈራል መመሪያ (ዳይሬክትሪ) በመጠቀም እየሠሩ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያለሪፈራል ወረቀት ተመላላሽ ታካሚዎችን የማይቀበሉ መሆኑን ገልፀው የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን በተመለከተ የወጣውን ደንብ ግን እንደማያውቁት አስረድተዋል፡፡

13. ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ-ምግባር መመሪያ (ethical and medico-legal regulation) ተዘጋጅተው ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ ጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የሥነ ምግባር መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑን ቢገልጹም የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ጊዜ ድረስ መረጃውን ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ኃላፊዎች ተጠይቀው ግን የሥነ ምግባር መመሪያው ስለመዘጋጀቱ አለማወቃቸውን ገልፀዋል፡፡

14. የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት በተሰጠ የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አገር አቀፍ የህሙማን አላላክና አቀባበል /ሪፈራል/ ስርዓት (የሆስፒታሎች የእርስ በእርስ ትስስር፣ በሆስፒታሎች ውስጥና በሆስፒታሎች መካከል ተናቦ መስራት ወዘተ) እንዲኖር እንዲሁም የህክምና ሥነ-ምግባር መመሪያ (ethical and medico-legal regulation) ተዘጋጅተው ተግባራዊ መደረጉን ተጠይቀው ሁሉም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ከመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያና ከአጠቃላይ ሆስፒታሎች ጋር በጥምረት እንዲሰሩ የተደረገ መሆኑን፣ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ (Ethical and Medco legal regulation) የፌዴራል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለሥልጣን (FMHACA) እየተዘጋጀ መሆኑን እንዲሁም የዜጎች ቲም ቻርተር ሁሉም የሪፈራል ሆስፒታሎች ወጥ በሆነ መልኩ እንዲያዘጋጁ ናሙና በጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው መላኩ ታውቋል፡፡

**የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ ታካሚዎችን አቀባበልና የሐኪሞች የጠዋት ስብሰባን በተመለከተ:-**

15. የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ታካሚዎችን የሚቀበሉት ጠዋት ብቻ መሆኑን፤ በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እቅድ መሰረት ሁሉም ታካሚዎች በ2 ሰዓት ውስጥ አገልግሎት የማያገኙ መሆናቸውን እና በአራቱም ኦዲቱ በተከናወነባቸው የሪፈራል ሆስፒታሎች (የቅዱስ ጳውሎስ፣ የጥቁር አንበሳ፣ የጅማ እና የጎንደር) የዶክተሮች የጠዋት ስብሰባ የሠዓት ገደብ የሌለ መሆኑ በተጨማሪም ከስብሰባ በኋላ በሻይ እረፍት ምክንያት ታካሚዎች ከ2 ሰዓት በላይ ዶክተሮችን የሚጠብቁ መሆኑን በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

16. በዚህም መሠረት የተመላላሽ ታካሚዎችን አቀባበል ለማቀላጠፍ እና የሆስፒታል ቆይታ ጊዜ ለመቀነስ ሆስፒታሎች ተመላላሽ ታካሚዎችን በማንኛውም የሥራ ሰዓት ሊቀበሉ እና ተመላላሽ ታካሚዎች የመጀመሪያ የህክምና አገልግሎት በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በተቀመጠው መሰረት በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሊያገኙ እንደሚገባ እና የሕክምና ዶክተሮች ለጠዋት የስብሰባ ጊዜያቸው የሰዓት ገደብ ሊያስቀምጡ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

17. ይሁን እንጂ የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ በናሙና ተመርጠው ኦዲት የተደረጉት ሦስቱም የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም::

18. በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በሁለቱ ሆስፒታሎች ታካሚዎችን በማንኛውም የሥራ ሠዓት ያለመቀበል ችግር አሁን ተሻሽሎ በማንኛውም ሠዓት አገልግሎት እንዲያገኙ የተደረገ መሆኑን በክትትል ኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የሐኪሞች የጠዋት የስበሰባ ጊዜ በተመለከተም በሆስፒታል የጤና ልማት ሠራዊት መመሪያ ውስጥ በግልፅ የሀኪሞች የጠዋት ስብሰባ ሠዓት እስከ 2፡30 ድረስ ብቻ ሆኖ ድንገተኛ ያልሆኑ ህሙማን ከ2፡30 ጀምሮ በሀኪሞች እንዲታዩ የተደረገ መሆኑን መ/ቤታችን ከ2003- እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

19. የሀኪሞች የጠዋት ስብሰባ ወጥ በሆነ መልኩ በሁሉም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች እንዲተገበር የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሁሉም ሆስፒታሎች የጠዋት ስብሰባ ከሦስት ሰዓት በፊት እንዲያልቅ በጤና ልማት መመሪያ ውስጥ አካቶ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተገበር አሰራጭቷል፡፡

**የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በምልክቶችና በቀለም መለየታቸውን በተመለከተ**

20. በኦዲቱ በታዩት አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ የህክምና ክፍሎችን ለመለየት የሚያስችሉ ምልክቶች በአግባቡ ያልተቀመጡና ምንም አይነት በቀለም የተለየ ክፍል ያለመኖሩ በኦዲት ወቅት ተረጋግጦ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ፣ የድንገተኛ እና የተኝቶ ህክምና ክፍሎች በቀላሉ ለማግኘት እንዲቻል ለታካሚው በግልፅ ሊታዩ በሚችል መልኩ ምልክቶች ሊቀመጡ እና ላልተማረ የህብረተሰብ ክፍል እንዲያመላክቱ ክፍሎቹ በቀለም ሊለዩ እንደሚገባ በኦዲት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

21. የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም፡፡

22. በክትትል ኦዲቱ ወቅት የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር የሆስፒታሎች የህክምና መስጫ ክፍሎችንና የአስተዳደር ክፍሎችን ማመልከቻ ሣይናጅ ምልክቶች ከህዝብ ተወካዮች ውይይት በኃላና የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባራዊ ባደረገው ፅዱ እና ምቹ ጤና ተቋማትን የመፌጠር ኢኒሼቲቭ በሁሉም ሆስፒታሎች የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና ቅልጥፍና እንዲሁም ተገልጋይ ተኮር እንዲሆን ክፍሎች ፅዱ ከመሆናቸው በተጨማሪ አቅጠጫ ጠቋሚዎችን እንዲኖር በማድረግ ደንበኛው በቀላሉ አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን እንዲያገኙ የተደረገ መሆኑን መሆኑን መ/ቤታችን ከ2003- እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

23. ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሳላይዝድ ሆስፒታል በሁሉም የህክምና ክፍሎች አካባቢ በግልፅ የሚታይ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች የተቀመጡ መሆኑን በክትትል ኦዲት ወቅት በተደረገ ምልከታ ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

ተመላላሽ ታካሚዎች የሚፈልጉትን የህክምና ክፍሎች በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል አመላካች ምልክቶች በድንገተኛ ክፍል በር ፊት ለፊት ከተቀመጠው ውጭ በሌሎች የላብራቶሪ፣ የራዲዮሎጅ እና የምርመራ ክፍሎች የሚያሳዩ አመላካች ምልክቶች አለመኖራቸው፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የድንገተኛና የላብራቶሪ ክፍሎች በትልልቅ የተፃፍ አመላካቾች ያሉ ቢሆንም በሌሎች የምርመራ ክፍሎች በየበሩ ላይ በትንንሹ የተለጠፈ ምልክቶች በመሆናቸው ከውጭ ወደ ግቢ ለሚገባ ተመላላሽ ታካሚ በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል አቅጣጫ ጠቋሚ ያልተቀመጠ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት በተደረገ ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

24. በመሆኑም ስለጉዳዩ የሚመለከታው የሆስፒታሉ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ማሻሻያ ትግበራ መመሪያ (Ethiopian Hospitals Reform Implementation Guideline, EHRG) ባስቀመጠው መልኩ ክፍሎችን በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል ምልክቶች የሌሉ መሆኑን ተቀብሎ ለወደፊት ግን እያንዳንዱ ክፍል ምልክት ሰጥተው መግቢያ በር ላይ ጠቋሚ /Index/ ፅሁፎችን ለማስቀመጥ ዲዛይን አሰርተው ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

### የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚመራና የሚከታተል የሆስፒታል ቦርድ በሁሉም ሆስፒታሎች መቋቋሙን በተመለከተ

25. የሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚመራና የሚቆጣጠር ቦርድ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እንዳልተቋቋመ፣ የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ግን በ2003 ዓ.ም ቦርድ ያቋቋመ መሆኑንና ቦርዱም በሰው ኃይል ፍላጎት ጥናትና በጤና አጠባበቅ ፋይናንስ (health care financing) አተገባበር ዙሪያ እየሠራ መሆኑን ሆስፒታሉም ስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም በሆስፒታሉ እና በዩኒቨርስቲው መካከል በቅንጅት ተናቦ የመስራት እና የማቀድ ችግሮች ያሉ መሆኑን በኦዲት ወቅት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

26. በመሆኑም አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተደራጀ የሆስፒታል እቅድ ለመስራት፣ የሂሳብ ቁጥጥር ለማድረግ፣ የሆስፒታሉ ንብረቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ እና አጠቃላይ የሆስፒታሉን የስራ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር/ለመከታተል፣ በጀት እና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ገምግሞ በማቅረብ የሚያስፀድቅ እንዲሁም በፀደቀው መሠረት መተግበሩን የሚከታተል የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ሊያቋቁሙ ይገባል በማለት በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

27. የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም፡፡

28. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በታዩት በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል ሆስፒታሎችን የሚመራና የሚቆጣጠር ቦርድ መቋቋሙ ታውቋል፡፡

29. በመሆኑም ሦስቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የራሳቸው የሆነ ቦርድ አቋቁመው ቦርዱም በአንዳንድ ውሳኔዎች ላይ የሚያግዛቸው መሆኑን የሆስፒታሎቹ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የገለፁልን ቢሆንም በጅማ ዩኒቨርሲት ሆስፒታል የተቋቋመ ቦርድ ግን ቶሎ ቶሎ ስለማይገናኝ ወቅታዊ ጉዳዮችን (ችግሮችን) ለመፍታት ብዙም ጥቅም አለመስጠቱን ገልጾዋል፡፡

**የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ**

30. የቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መደበኛ ክትትልና ድጋፍ የሚያገኝ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መደበኛ ባይሆንም አልፎ አልፎ ክትትል እና ድጋፍ የሚያገኝ ቢሆንም ከትምህርት ሚኒስቴር ግን የቴክኒክ ድጋፍም ሆነ ክትትል የማያገኝ መሆኑ እንዲሁም የጎንደርና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ ከትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ ክትትል የማያገኙ መሆኑን፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችንና የህክምና መገልገያ ቁሣቁሶችን አቅርቦትና አጠቃቀም በመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ እና የመድኃኒትና የጤና አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለሥልጣን (FMHACA) አማካኝነት ክትትል የሚያደርግ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የጅማና የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች በዚህ ዙሪያ ከየትኛውም አካል መደበኛ የሆነ ክትትልና ድጋፍ የማያገኙ መሆኑን፣ የዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ በየትኛውም አካል በባለቤትነት አለመያዙ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል የሚመጡ ድጋፎችን በመደበኛነት ባለማግኘታቸው የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች እጥረት፣ አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና መሳሪያዎች ሳይወገዱ ለብዙ ጊዜ በመጋዘን ውስጥ የመከማቸት ችግሮች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጦ ነበር፡፡

31. በዚህም መሠረት በዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች አስፈላጊ መድሃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም እንዲሁም አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚከታተል እና ድጋፍ የሚያደርግ ክፍል በትምህርት ሚኒስቴር ስር ሲቋቋም፣ ትምህርት ሚኒስቴር እና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን እና የማስተማርና የምርምር ስራውን በቅንጅት እንዲከታተሉና እንዲቆጣጠሩ የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት (memorandum of understanding) ሊኖራቸው የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

32. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በጤና-ጥበቃ ስር የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚከታተል የክልኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የተቋቋመ መሆኑን፣ ትምህርት ሚኒስቴር እና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን እና የማስተማርና የምርምር ስራውን በቅንጅት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የመግባቢያ ስምምነት (memorandum of understanding) ተፈራርሟል፣ በዚህም መሰረት የክትትል ኦዲት ከተደረገባቸው ሦስት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በትምህርት ሚኒስቴር በሁለቱም ሚኒስቴር መ/ቤቶች በቅንጅት ክትትልና ድጋፍ የሚደረግላቸው መሆኑን የሁለቱ ሆስፒታሎች የበላይ ኃላፊዎች የገለጹልን ሲሆን የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ግን ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አሁንም ቢሆን ምንም ዓይነት ክትትልና ድጋፍ የማይደረግላቸው መሆኑን የሆስፒታሉ ኃላፊ ተጠይቀው ገልጸዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለሆስፒታሉ የተቻለውን የሥልጠናና ሌሎች ድጋፍ እንደሚደርግ የገለጸ እና በቅርቡ ከ3.5 ሚሊዩን ብር በላይ የሚያወጡ መድኃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች ለሆስፒታሉ በእርዳታ እንዲያገኝ ያደረገበትን ማስረጃ ለረቂቅ ክትትል ኦዲት ሪፖርቱ ከሰጡት ምላሽ ጋር በአባሪነት አያይዘው አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የላቦራቶሪ ግብዓቶችን እና መመሪያዎችን በተመለከተ፤

34. የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላብራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የተለየ መመሪያ የሌለው መሆኑ፣ በቂ የላብራቶሪ ክፍል፣ ናሙና መቀበያ ቦታ እና የግብአት አቅርቦት ችግር መኖራቸውን እንዲሁም የ'ኬሚስትሪ ባክአፕ' እና 'ዩፒኤስ' እጥረት መኖሩን፣ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የላቦራቶሪ ጥራት መመሪያ፣ የላቦራቶሪ ባዮ ሴፍቲ መመሪያ እና ለማህበረሰብ የጤና ላቦራቶሪዎች የጤና እና ደህንነት መመሪያዎች ቢኖሩም በመመሪያው መሰረት ሙሉ በሙሉ እንዳልተተገበሩ በኦዲቱ ወቅት የላቦራቶሪ ኃላፊዎችን በመጠየቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሆስፒታሉ የላቦራቶሪ ግብዓት እጥረት (reagent, hormone analyzer)፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እጥረትና በቂ ቦታ ባለመኖሩ የካንሰር ምርመራ መስራት ያልቻሉ መሆኑን፣ በጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላብራቶሪ ናሙና አሰባሰብን በተመለከተ ፖሊሲ እና መመሪያ ቢኖርም የሆስፒታሉ ላብራቶሪ የሪኤጀንት እና ማቅለጫዎች አቅርቦት ችግር፣ የላብራቶሪ ቁሣቁሶች እጥረት፣ የናሙና መጓጓዣ ችግር፣ የናሙና መሰብሰቢያ ቅፅ ላይ ሙሉ የሆነ የታካሚ መረጃ ያለመሙላት፣ የናሙና እና የውጤት አያያዝ ችግሮች ማለትም ያለቦታ የማስቀመጥ፣ ቦታውን መቀየር እና የናሙና ውጤት መጥፋት ችግሮች ያሉ መሆኑን በጠቃላይ የላብራቶሪ መመሪያዎች ባለመቀረፃቸው እና የተቀረፁትም ሙሉ ለሙሉ አለመተግበራቸው፣ የተሟላ የግዥ ዕቅድ ባለመኖሩ እንዲሁም ለላቡራቶሪ ማሽኖቹ መለዋወጫ እና ሪኤጀንቶች ባለመሟላታቸው የአገልግሎት መቋረጥ ችግር መኖሩ፣ ታካሚዎች ወደ ግል ላቦራቶሪዎች እንዲሄዱ መገደዳቸው እንዲሁም ሆስፒታሎች የላብራቶሪ ውጤት እንደደረሰ የማይሰጡ በመሆኑ ታካሚዎችን ለአላስፈላጊ እንግልት፣ መዘግየት እና ለተጨማሪ ወጭ እንዲሁም የተገልጋዩን ፍላጎት ማሟላት እንዳይቻል ማድረጉ በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

35. በዚህም መሠረት የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ እና በመመሪያው መሰረት ሊሰራ እንዲሁም ሆስፒታሉ ምቹ የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጫ ቦታ፣ እንደታካሚው ብዛት ተመጣጣኝ የኬሚስትሪ ማሽንና ባክ-አፕ (Back Up) ሊኖረው የሚገባ መሆኑን፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታልና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የላብራቶሪ ሪኤጀንትና አናላይዘርስ አቅርቦት ችግርን፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እጥረትን፣ የላብራቶሪ ውጤት መጥፋትና የታካሚን ሙሉ መረጃ ያለመሙላት ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ሊሰጡ የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥተው ነበር፡፡በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት

ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

36. አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌደራል ሪፌራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲትር መ/ቤት አላኩም፡፡

37. የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር እና የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አስተዳደርና የትምህርት ክፍሉ በወሰዱት ጠንካራ እርምጃ የላብራቶሪ ክፍሉ ካለበት የአሰራር የኣስተዳደርና የግብዓት ችግሮች በመውጣት ባለአራት ኮኮብ ላብራቶሪ ተብሎ የተሸለመ መሆኑን፤ በአገር አቀፍ ደረጃ በላብራቶሪ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን ችግር በተከታታይ በማጥናት መፍተሔ የሚሆን አሰራር በመዘርጋቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የላብራቶሪ ግብዓቶች የፍላጎት ዳሰሳ ተከናወኖ ሆስፒታሎቹም የሦስት አመት ፍላጎታቸውን እንዲያሳውቁ የተደረገ መሆኑን እንዲሁም ለአራቱ ሆስፒታሎችም ዘመናዊ የሆነ በአንድ ጊዜ እስከ 400 ናሙና መሥራት የሚችሉ መሳሪያዎችም የተሰጠ ቢሆንም በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት እስከ አሁን ድረስ የሚፈለጉት ግብዓት ሙሉ በሙሉ ያልተሟሉ በመሆኑ፣ ችግሩን ለመቅረፍ የደጀን ላብራቶሪ ተቋቁመው ሥራ የጀመረ በመሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎቱን ከግል ተቋማት እንዲያገኙ የሚደረጉ መጉላላት በእጅጉ እንዲቀንስ ማድረጉን  መ/ቤታችን ከ2003- እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

38. የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ መመሪያ አዘጋጅተው በመመሪያው መሰረት እየሰሩ መሆናቸው፣ እንዲሁም ሶስቱም ሆስፒታል ምቹ የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጫ ቦታና ተመጣጣኝ የኬሚስትሪ ማሽንና ባክ-አፕ (Back Up) የተሟለላቸው መሆኑን እና የላብራቶሪ ውጤት መጥፋትና የታካሚን ሙሉ መረጃ ያለመሙላት ችግሮች በሙሉ በሦስቱም ሆስፒታሎች መሻሻል ማሳየታቸው በክትትል ኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ በሦስቱም ሪፈራል ሆስፒታሎች የሪኤጀንትና አናላይዘርስ አቅርቦት ችግር ያልተፈታ በመሆኑ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በደጀን ላብራቶሪ (በጋራ የሚያገለግል ላብራቶሪ) አገልግሎት የሚያገኙ ሲሆን የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ግን የደጀን ላብራቶሪ በአካባቢ ባለመኖሩ ተመላላሽ ታካሚዎች ወደ ግልና አዲስ አበባ ወደ ሚገኙ ሆስፒታሎች በመላክ አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ በመሆኑ ላለአስፈለጊ ወጪ እና

እንግልት የሚደረጉ መሆኑን የሆስፒታሉ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

39. ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች አስመልክተው ጉዳዩ የሚመለከተው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሪኤጀንት አቅርቦት እጥረት የቆሙ የህክምና መሣሪያዎች አዲስ አበባ ላሉት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በቀረቡት ጥያቄ መሰረት ግዥ እየተፈፀመላቸው ችግሮችን ለማቀላል እየተሞከረ መሆኑንና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያሉት የህክምና ማሽኖች ግን አሮጌ በመሆናቸው መለዋወጫና ሪኤጀንት ለማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በዝርዝር እንዲያሳውቁ አቅጣጫ የተሰጣቸው መሆኑን አስረድቷል፡፡

**በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡ ትምህርት እና ስልጠናዎች የሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዱ መሆናቸውን በተመለከተ፡-**

40. ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እና በጅማ ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል የህክምና እና የማስተማር አገልግሎት ላይ የትኛው ቅድሚያ ማግኘት አለበት በሚለው ዙሪያ ግልፅ የሆነ አሰራር አለመኖር ይህም በህክምና ዶክተሮች መሀከል እያከሙ ማስተማር (ለህክምና አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት) ወይንም እያስተማሩ ማከም (ለትምህርትና ስልጠናዎች ቅድሚያ መስጠት) የሚል ግልፅ የሆነ የግንዛቤ እጥረቶች መኖራቸው፤ ይህንንም ለመወሰን የተዘጋጀ ግልፅና ወጥ መመሪያ ያለመኖሩ፤ እንዲሁም ሃኪሞች የስራ ሰዓታቸውን ለሆስፒታሉ አገልግሎት ብቻ የሚያውሉ መሆኑን የሚከታተሉበትና የሚቆጣጠሩበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ በኦዲት ወቅት ተረጋግጦ ነበር፡፡

41. በዚህም መሠረት አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የትምህርት /ሥልጠና ጊዜ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥን በማይጎዳ መልኩ ሊያስኬዱ እና የሀኪሞችን የሰዓት ክፍፍል ለይተው ሊያስቀምጡ፣ እንዲሁም በሪፖርት፣ በሳምንታዊ እቅድና ክንውን፣ በትምህርት ክፍል ኃላፊዎች አማካኝነት ወዘተ የህክምና ዶክተሮችን በስራ ሰዓት ሊከታተሉ የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

42. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው የጤና-ጥበቃ ሚኒስትርም ሆነ አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም፡፡

43. የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር በአጠቃላይ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል/ዩንቨርሲቲ/ ሆስፒታል አሰራርና ማኔጅመንት ብሎም የአገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የፌዴራል /የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ማኔጅመንት መመሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ከተዘጋጀ በኃላ በጤና-ጥበቃና በትምህርት ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች ተፈርሞ የፀደቀ ሲሆን ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ተልኮ ወደ ትግባራ የገቡ መሆኑን እንዲሁም አተገባበሩ ላይም ቀጣይ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን ሐኪሞች ተግባራቸውን የሚፈፅሙበት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት እንድፈፅሙ ከሆስፒታሎቹ የሥራ ኃላፊዎችና ሐኪሞች ጋር ውይይት የተደረገ መሆኑን መሆኑን መ/ቤታችን ከ2003-እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

44. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲት ወቅት የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና በጅማ ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል የህክምና እና የትምህርት/ሥልጠና ጊዜ ወጥ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠ ምንም ዓይነት መመሪያ የሌለ መሆኑን የሆስታሎቹ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

45. የህክምና እና የትምህርት/ሥልጠና ጊዜ ወጥ በሆነ ሁኔታ ተለይተው አገልግሎት የማይሰጥበትን ምክንያት አስመልክተው ጉዳዩ ለሚመለከተው የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች መተዳደሪያ ደንብ ላይ የእያንዳንዱ ሀኪም ተግባር ምን እንደሆነ የተገለፀ መሆኑን ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸው ሴኔት ስላላቸው በጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር ብቻ ወጥ የሆነ መመሪያ ማዘጋጀት የማያስፈልግ መሆኑን እንዲሁም አንዳንድ ሙያዎች ሙሉ በሙሉ እያከሙ ማስተማር በመሆኑ ከሙያ ሙያ የሚለያይ ሲሆን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም በማስተማር ዙርያ ሙሉ በሙሉ ስልጣን የሌለው መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ይስጡ እንጂ በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ የተጠቀሰውን ግኝት በተመለከተ የተቀናጀ መመሪያ አለመኖሩን እንደችግር ከተቀበሉት የተለየ አዲስ ሃሳብ ማቅረባቸው እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሥርዓቱን ማስቀመጥ ስለሚቻል የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

**በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዘመናዊና በቂ የሆነ የህክምና እና የምርመራ መሳሪያዎች መኖራቸውን በተመለከተ**

46. የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ‘ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ’ (MRI) ማሽን የሌለ እና የኬሚሰትሪ ማሽን እጥረቶች ያሉ መሆኑን ፣ሆስፒታሉ የህክምና መሳሪያዎች

ጥገና ክፍል (bio-medical engineering department) የተቋቋመ ቢሆንም የሚሰጠው አገልግሎት ከሆስፒታሉ ፍላጎት አንፃር በቂ ያለመሆኑ እና የቅድመ መከላከል ፍተሻ አገልግሎት እንደማይሰጥ፣ የአንዳንድ መሳሪያዎች ግዥ ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚፈፀም በመሆኑ የጥገናውንም አገልግሎት የሚሰጠው አቅራቢው ብቻ በመሆኑ ሙሉ የጥገና አገልግሎት ለማግኘት የሚዘገይ መሆኑን፣

47. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል በቂ የህክምና እና የምርመራ መሣሪያዎች የሌሉት መሆኑን፣ የላብራቶሪ ማሽኖች ለምሳሌ ሆርሞን አናላይዘር፣ ቫይራል ሎድ፣ ፋክስ ካሊበር፣ 5DF፣ ሄማቶሎጂ እና የምርመራ መሣሪያዎች እንደ 'ሲቲስካን' (CT-Scan) የተከላ ስራው ቢጀመርም ያልተጠናቀቀ መሆኑን፤ 'ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ' (MRI) በከፍተኛ ወጪ ግዥ ቢፈፀምም የማሽኑ ማስቀመጫ ቦታ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ምክንያት እስከ አሁን ያልተተከለ መሆኑን፣ ማሞግራፍ፣ የመሳሰሉት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን በተጨማሪ የአልትራሳውንድ ማሽን ከአሥር ዓመት በፊት ጀምሮ ያለ ሲሆን በራጅ ክፍል የራጅ ወረቀት ማድረቂያው በቂ ባለመሆኑ ፊልሙን ለማንበብ ብዙ ሰዓት የሚወስድ መሆኑን፣የህክምናና የምርመራ መሣሪያዎች ከአገልግሎት በፊት ፍተሻ የሚደረገው በሆስፒታሉ የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ መሆኑን፣ ከዚህም ውስጥ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን በላብራቶሪ ባለሙያዎች አማካኝነት ሲሆን ከአገልግሎት በኋላ ግን በዚህ ዙሪያ የሰለጠኑ ባለሙያዎች የሌለ መሆኑን፣

48. በተመሳሳይ በጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል የሕክምና እና የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ከተጠቃሚዎቹ አንፃር ሲታይ በቂና ዘመናዊ አለመሆናቸው፣ ሆስፒታሉም የጥገና ክፍል የሌለው መሆኑን እንዲሁም የሆስፒታሉ ላውንደሪ ማሽንም ባለመጠገኑ ምክንያት እስከ ግንቦት 2004 የማይሰራ መሆኑን በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡

49. በዚህም መሠረት በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩት አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊና በቂ የሆነ የህክምና ምርመራ መሣሪያዎች ሊኖራቸው እንዲሁም መሳሪያዎቹ መደበኛ የቅድመ ምርመራ ፍተሻ እና ከአገልግሎት በኋላ ጥገና ሊደረግላቸው የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር።

50. የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ

የሚወስዱበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም፡፡

51. ጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዘመናዊና በቂ በሆነ የህክምና እና የምርመራ መሳሪያዎች ማለትም (CT-Scan, MRI, Digital X-ray) ድንገተኛ ህክምና (Mechanical, ventilator, Defibrillator, section Machine, portable X-ray, starchier, Wheelchair, oxygen concentrator) የቀዶ ህክምና (Operating table, OR Light, anesthesia machine, Surgical sets) የወሊድና የጨቅላ ህፃናትን አገልግሎት ለማሻሻል (Delivery coach, incubator, phototherapy, re-suscitation sets etc.) ፓኬጅ በማዘጋጀት ለሆስፒታሎች የተሰጡ መሆኑን ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ ሆስፒታሎች ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ግዥ የፈፀመ መሆኑን መሆኑን መ/ቤታችን ከ2003- እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

52. በክትትል ኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው

- ከሶስቱ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል እና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ሁለቱም ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎች የተሟላላቸው በመሆኑ በመሣሪያ እጦት እጥረት ወደ ውጭ የሚላኩ ተመላላሽ ታካሚዎች የሌላቸው መሆኑን፣
- በሦስቱም ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎች ጥገና ክፍል (bio-medical engineer-ing department) ተቋቋመው የህክምና መሣሪያዎችን ደህንነት በየቀኑ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን
- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በብሔራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት አማካኝነት ማሳሪያዎችን ዓመታዊ ፍተሻ(Calibration) እያስደረገ ሠርትፍኬት የሚቀበል መሆኑን፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በገለልተኛ አካል ፍተሻ( Calibration) የማያስደርጉ መሆኑን የሆስፒታሉ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አስፈላጊ የሆኑ የህክምና መሣሪያዎች ማለትም፤-ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ (MRI) እና ዘመናዊ ሲቲ ስካን ግዥ ተፈፅሞ በአዲሱ የሆስፒታሉ ህንፃ ውስጥ ለመትከል ዝግጅት ላይ መሆናቸውን የገለጹልን ሲሆን፣ ቢተከልም ግን ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል መሣሪያውን

ለማንቀሳቀስ በቂ አለመሆኑ፣ ችግሩ እስኪቀረፍ ታካሚዎች ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ወደ ሌላ ሆስፒታሎች ሪፈር የሚደረጉ መሆኑን እንዲሁም የሆስፒታሉ የራዲዮሎጂ ክፍል አንድ ራዲዮሎጂስት በለሙያ እና ሁለት የኤክስሬና ሁለት የአልትራሳውንድ የዱሮ/የቆዩ/ ማሽኖች ብቻ ያሉ በመሆኑ ካለው ታካሚ ብዛት አንፃር ቁጥራቸው አነስተኛ ስለሆነ ታካሚዎች በፍጥነት አገልግሎት የማያገኙ መሆኑን፣ ተበላሽቶ የነበረው የሆስፒታሉ ላውንደሪ ማሽንም የማይሰራ መሆኑ በክትትል ኦዲት ወቅት በተደረገው የመስክ ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**በቂ የሆነ የመፀዳጃ ቤት፣ 24 ሰዓት የውሃና የመብራት አገልግሎት እና የኢንፌክሽን መከላከል ክፍል መኖሩን በተመለከተ**

53. በጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተመላላሽ ታካሚዎችን ቁጥር ያገናዘበ የመፀዳጃ ቤት የሌለ መሆኑን፣ ለታካሚዎች በቂ የማረፊያ ቦታ የሌለ መሆኑን፣ በሆስፒታሉ የስትሬቸር እጥረት መኖሩን፣ የውሃ አቅርቦት ችግር በመኖሩ ከ6ኛ-8ኛ ፎቅ ውሃ የማይደርስ መሆኑ፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከፍተኛ የመፀዳጃ ቤት ችግር ያለ መሆኑ፣ የጅማና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች የኢንፌክሽን መከላከያ ክፍል ያልተቋቋመ እንዲሁም የኤሌክትሪክ መቆራረጥ እና በቂ የመፀዳጃ ቤቶች አለመኖራቸው በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡

54. በዚህም መሠረት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች እንደታካሚው ብዛት ተመጣጣኝ መፀዳጃ ቤቶች ሊኖራቸው፣ በተደጋጋሚ የውሃና የመብራት መቆራረጥ ችግሮችን እንደየአስፈላጊነቱ ተለዋጭ/ተጠባባቂ አገልግሎቶችን በመጠቀም መፍትሔ ሊበጅ፣ በቂ የሆነ የታካሚዎች ማረፊያ ቦታ ሊዘጋጅ የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

55. የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላኩም፡፡

56. ጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር የውሃና የመብራት ኃይል መቆራረጥ ሙሉ በሙሉ የተወገደ ባይሆንም ሆስፒታሎች የራሳቸው ባክ አፕ ጄኔሬታሮች እንዲያዘጋጁ የተደረገ መሆኑን፤በየሆስፒታሎች ዋና ችግር የነበረው የመፀዳጃ ቤቶች በበቂ ሁኔታ ያለመኖር እና የንጽህና አያያዛቸው ጉዳይ ላይ ያተኮረ ፅዱ እና ምቹ ጤና ተቋማትን የመፍጠር ጎራ ንቅናቄ የተፈጠረ መሆኑን፤ ፅዱና ምቹ ጤና ተቋማት የመፍጠር ኢኒሼቲቭ በሁሉም ደረጃ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና ቅልጥፍና እንዲሁም ተገልጋይ ተኮር

እንዲሆን መሰረታዊ የሆነ የአመለካከት ለውጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲመጣ በከፍተኛ ትኩረትና ክትትል የሚተገበር የአገልግሎት ማሻሻያ ኢኒሼቲቭ የተደረገ መሆኑን፤

57. የዚህ ኢኒሼቲቭ ዋና ዓላማ ፅዱና ምቹ ጤና ተቋማት በመፍጠር የጤና ተቋማት ገጽታን በመገንባት እንዲሁም ተገልጋዮች፣ጠያቂዎች እና አገልግሎት ሰጪዎች ደህንነት መጠበቅ ሲሆን ዝርዝር ዓላማው ጤና ተቋመት ለተገልጋዮች፣ ለጠያቂዎች እና አገልግሎት ሰጭዎች ምቹ ማድረግ የጤና ተቋማት የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት፣ በጤና ተቋማት ፅዳት ዙሪያ ሁሉን አቀፍ ንቅናቄ መፍጠር እና የጤና ተቋማት የብክለት መከላከል እና የህሙማን ደህንነት ስታንዳርዶች ትግበራ ማሻሻያ የተደረገ መሆኑን፣ በዚህ ከፍተኛ ህዝብ ንቅናቄ ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ መሻሻሎች በሁሉም ሆስፒታላችን በመፈጠሩ ይህንን ጉዳይ በቀጥታ በመከታተል ድጋፍ የሚያደርግ ከፍተኛ የመንግስት አመራሮችና ተዋቂ ግለሰቦች የንቅናቄው አምባሳደር ተደርገ የተሸሙ መሆኑን መሆኑን መ/ቤታችን ከ2003- እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

58. በክትትል ኦዲትም ወቅት

- ጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የመብራት ችግር መጠባበቂያ (ስታንድ ባይ) ጀኔሬተርና መረጃ እንዳይጠፋ ዘመናዊ ዩፒ-ኤስ በየክፍሉ በማዘጋጀት ችግሩን የፈቱ መሆኑ፣
- ውሃን በተመለከተ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በቂ የውሃ ክምችት ያላቸው ሲሆን ጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከህንፃ ግንባታ አሰራር ችግር የተነሳ እስከ ስድስተኛ ፎቅ ድረስ የማይሄድ መሆኑንን፣ ጅማ ዩኒቬርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የውሃ ችግር በመኖሩ በቀን የሚያቀርብላቸው ቦቴ መኪና ኮንትራት ተኮናትረው በየቀኑ የሚያመላልሰላቸው መሆኑ ነገር ግን የውሃ ችግር ግን በአዲሱ ሆስፒታል ላይ ሲገቡ የሚቀረፍላቸው መሆኑን፤፤
- የጅማ ሆስፒታል አዲስ ወደ ተሰራው ህንፃ ውስጥ ለመግባትና ዘመናዊ የህክምና መሣሪያዎችን እና የላውንደሪ ማሽኖችን ለመጠቀም የሚያስችል በቂ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት አለመኖሩ፣
- የመፀዳጃ ክፍሎችን በተመለከተ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል ለተመላላሽ ታካሚዎች ለብቻ አስራ ስድስት(16) መፀዳጃ ቤቶችን በማስገንባት አገልግሎት

እንዲያገኙ ማድረጉ፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሌኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ግን የቦታ እጥረት በመኖሩ ምክንያት ተጨማሪ ግንባታ ለማካሄድ ያልቻሉ መሆኑን እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አዲስ ህንፃ ላይ በቂ መፀዳጃ ቤቶች ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ ስለሆነ ለወደፊት ችግሩን የሚፈታላቸው ቢሆንም ግን አሁን ባለው ደረጃ ከፍተኛ የመፀዳጃ ቤት ችግር መኖሩን

በክትትል ኦዲቱ ምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**የሚከታተል የመድሃኒት እና ቴራፔቲክ ኮሚቴ (Drug and Therapeutic Committee) መቋቋሙን በተመለከተ**

59. የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የመድኃኒትና ቴራፔቲክ ኮሚቴ በ2003 ዓ.ም ቢያቋቁሙም በሙሉ አቅሙ እየሰራ እንዳልሆነ እንዲሁም በሆስፒታሉ ፋርማሲዎች በቂና አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች አቅርቦት ችግር መኖሩ ታውቋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በቅዱስ ጳውሎስ፣ በጅማና ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች በ2003 መጨረሻ አካባቢ ኮሚቴው የተቋቋመ ቢሆንም የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት በአግባቡ ያልተደራጀ መሆኑን እንዲሁም የሆስፒታሉ ፋርማሲዎች አስፈላጊ መድሃኒቶችን በበቂ ሁኔታ ባለመያዛቸው ምክንያት ታካሚዎች ወደ ግል ፋርማሲዎች ስለሚላኩ ለተጨማሪ ወጪ፣ ለአላስፈላጊ መዘግየት እና የታካሚዎችን ፍላጎት ያለማሟላት ችግሮች መኖራቸውን በኦዲት ግኝቱ ተረጋግጦ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚገኙት የመድኃኒትና ቴራፕዩትክ ኮሚቴዎች (DTCs) የአስፈላጊ (essential) መድኃኒቶችን ዝርዝር ዝግጅት፣ አቅርቦት፣ ግዥ፣ አጠቃቀምና ቁጥጥር በሚገባ ሊፈፅሙ በሚችሉ መልኩ ሊጠናከሩ ይገባል በማላት በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባ ነበር፡፡

60. ጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርና አራቱም ኦዲት የተደረጉት የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅተው ለመ/ቤታችን አላኩም፡፡

61. በሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ሰነድ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ሥራዎች አንዱ ሁሉም የመንግስት ጤና ድርጅቶች የፋርማሲ አገልግሎት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ማድረግን ተሰቢ ያደረገ በመሆኑ በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የፋርማሲ አገልግሎት ተጠያቂነት ያለው የመድሃኒት አገልግሎት እንዲጀምሩ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ትግበራ የገቡ መሆኑን ከዚህ ጋር በመያያዝ የትራፒዩትክ ኮሚቴዎች በአዲስ መልክ እንዲጠናከሩ የተደረገ በመሆኑን እነዚህ ኮሚቴዎችም ለየሆስፒታላቸው የሚሆኑ መድሃኒቶች የለዩ ሲሆን

የሦስት ዓመት ፍጆታም ያዘጋጁ መሆኑን መሆኑን መ/ቤታችን ከ2003- እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ በመ/ቤታችሁ ላይ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የወሰዳችሁትን እርምጃ አሳውቁ በማለት በጠየቅነው መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር፡-መወ8/45/401 በቀን 30/06/2008 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን በላከው ምላሽ ላይ ገልጿል፡፡

62. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ሦስቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የመድኃኒትና ቴራፒዩትክ ኮሚቴዎች (DTCs) ተቋቁመው አስፈላጊ የሆኑ የመድኃኒቶችን ዝርዝር የሚያዘጋጁ እና ኦዲተብል ፋርማሲ እየተተገበረ ሥራ የጀመሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

63. በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ አገርቱ ያወጣችውን አገር አቀፍ የሪፈራል ስርአት ደንብ እና ጤና ጥበቃ ሚንስቴር ያዘጋጀውን የሪፈራል መመሪያ (ዳይሬክትሪ) በመጠቀም እንደሚሰሩ፣
- የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ እና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተመላላሽ ታካሚዎችን በማንኛውም የሥራ ስዓት የሚቀበሉ እና የሀኪሞች የጠዋት ስብሰባ ከሁለት ሠዓት ከሠላሣ(2፡30) ደቂቃ በፊት ተጠናቆ ከሁለት ሠዓት ከሠላሣ ደቂቃ በኃላ ሁሉም ሀኪሞች ሥራቸው ላይ እንዲገኙ የሚያደርግ በጤና ልማት ሠራዊት ግንባታ መመሪያ ውስጥ ተካቶ የተዘጋጀ እና በሦስቱም ሆስፒታሎች ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ፣
- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሳላይዝድ ሆስፒተል በሁሉም የህክምና ክፍሎች አካባቢ በግልፅ የሚታይ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች መኖራቸው፣
- የክትትል ኦዲት በተደረገባቸው በሦስቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የራሳቸው የሆነ ቦርድ ያቋቋሙ መሆኑ፣
- በኦዲቱ ሪፖርቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ትምህርት ሚኒስቴር እና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን እና የማስተማርና የምርምር ስራውን በቅንጅት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የመግባቢያ ስምምነት (memorandum of understanding) የተፈራረሙ መሆኑን፣
- የክትትል ኦዲት ከተደረገባቸው ሦስት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም

ሜዲካል ኮሌጅ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በትምህርት ሚኒስቴር በቅንጅት ክትትልና ድጋፍ የሚያገኙ መሆኑ፣

- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ችግሩን ለመቅረፍ በተቋቋመው በደጀን ላብራቶሪ (በጋራ የሚያገለግል ላብራቶሪ) አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን፣
- በኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሦስቱም ሪፈራል ሆስፒታሎች የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑን፣ ምቹ የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጫ ቦታ፣ እንደታካሚው ብዛት ተመጣጣኝ የኬሚስትሪ ማሽንና ባክ-አፕ (Back Up) በየክፍሉ የተዘጋጀ መሆኑን እና የላብራቶሪ ውጤት መጥፋትና የታካሚን ሙሉ መረጃ ያለመሙላት ችግሮችን መሻሻል መታየቱ፣
- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል እና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ሁለቱም ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎች የተሟላላቸው በመሆኑ በመሣሪያ እጦት አጥረት ወደ ውጭ የሚላኩ ተመላላሽ ታካሚዎች የሌላቸው መሆኑ፣
- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በብሔራዊ የስነልክ ኢንስቲትዩት አማካኝነት መሳሪያዎችን ዓመታዊ ፍተሻ (Calibration) የሚያደርግ መሆኑን፣
- ጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የመብራት ችግር ስታንድ ባይ ጄኔሬተርና የፒ-ኤስ በየክፍሉ በማዘጋጀት ችግሩ የተስተካከለ መሆኑ፣
- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የውሃ እጥረት ችግር ለመቅረፍ ሥራዎች የተሰሩ መሆኑን፣
- የመፀዳጃ ክፍሎችን በተመለከተ፡- ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለተመላላሽ ታካሚዎች ለብቻ አስራ ስድስት (16) መፀዳጃ ቤቶችን በማስገንባት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አዲስ ባሰራው ሕንጻ ውስጥ ተጨማሪ የመጸዳጃ ቤቶች የሰራ መሆኑ፣
- በሦስቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የመድኃኒትና ቴራፒዩትክ ኮሚቴዎች (DTCs) ተቋቁመው አስፈላጊ የሆኑ የመድኃኒቶችን ዝርዝር መዘጋጀቱና ኦዲተብል ፋርማሲ ተግባራዊ ተደርጎ ሪፖርት የሚያቀርቡ መሆኑን፣

ታውቋል፡፡

## 3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ በናሙና ተመርጠው ኦዲት የተደረጉት ሦስቱም የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር ያላኩ መሆኑ፣
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያለሪፈራል ወረቀት ተመላላሽ ታካሚዎችን የማይቀበል ቢሆንም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን በሚመለከት የወጣውን ደንብ ግን የማያውቀው መሆኑ፣
- በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የህክምና ክፍሎች በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል አመላካች ምልክቶች በድንገተኛ ክፍል ፊት ለፊት ያለ ቢሆንም የላብራቶሪ፣ የራዲዮሎጅ እና የምርመራ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መለያ ምልክት አለመኖሩ፣
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የድንገተኛና የላብራቶሪ ክፍሎች በቀላሉ ለመለየት የሚያስችሉ በትልልቅ የተፃፉ አማላካቾች ያሉ ቢሆንም ሌሎች የምርመራ ክፍሎችን ለማግኘት የሚያስችል አማላካች ምልክቶች አለመዘጋጀታቸው፣
- በክትትል ኦዲት ወቅት በሦስቱም ሪፈራል ሆስፒታሎች በሪኤጀንት አቅርቦትና በመለዋወጫ ዕቃ እጥረት ምክንያት የህክምና መሳሪያዎች አገልግሎት የቆሙ መሆናቸው፣
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል  የደጀን ላብራቶሪ የማያገኝ መሆኑ፣
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል አስፈላጊ የሆኑ የህክምና መሣሪያዎች ማላትም፣-ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ (MRI)፣ ዘመናዊ ሲቲስካን ግዥ የተፈፀመ ቢሆንም በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ባለመኖሩ መሳሪያዎቹ ሥራ አለመጀመራቸው፣
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በገለልተኛ አካል የሚገለገሉባቸውን የህክምና መሳሪያዎች ፍተሻ (Calibration) የማያስደርጉ መሆኑ፣
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አዲስ ወደ ሰራው ህንፃ ለመግባት ዘመናዊ የህክምና እና ላውንደሪ ማሽኖችን ለመጠቀም የሚያስችል የመብራት ጉልበት አለመኖሩ፣
- በጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተበላሽቶ እሰከ ግንቦት 2004 ድረስ ያልተጠገነው የላውንደሪ ማሽን የክትትል ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተጠግኖ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣
- ጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከህንፃ ግንባታ አሰራር ችግር የተነሳ እስከ ስድስተኛ ፎቅ ድረስ ውሃ የማይሄድ መሆኑን፣

- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ የመፀዳጃ ቤቶች እጥረት እስከአሁን መኖሩን ታውቋል፡፡

Office of the Federal Auditor General

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

64. ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍል ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት በሚመለከታቸው አካለት (የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር እና በናሙና በታዩ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች) የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

65. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የእርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሚመለከታቸው በሁሉም አካላት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ እና በናሙና የታዩት የሦስቱ ሪፈራል ሆስፒታሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡